**የአውሮፓ ሕብረት**
**የምርጫ ታዛቢ ልዑክ በኢትዮጵያ 2002 ዓ.ም.**
**የሕዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ**

**ለአስቸኳይ መግለጫ**

**ጋዜጣዊ መግለጫ**

**አዲስ አበባ ግንቦት 06 2002ዓ.ም.**

## የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ዋና ታዛቢ ቲዝ በርማን ወደ ኢትዮጵያ ሊመጡ ነው፡፡

የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ዋና ታዛቢ ቲዝ በርማን ሰኞ ግንቦት 09/2002 ዓ.ም. ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ ይገባሉ፡፡ ዋና ታዛቢ ቲዝ በርማን የአውሮፓ ህብረት የፓርላማ አባል ሲሆኑ 170 የሚሆኑ ታዛቢዎችን መርተው አዲስ አበባ የገቡት ሚያዚያ 7 ቀን 2002 ዓ.ም ነበር፡፡

“የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች እዚህ መኖር ለምርጫው ሂደት ተአማኒነትና ተቀባይነት አስተዋፅኦ ያደርጋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን” ብለው ነበር ወደ አውሮፓ ከመሄዳቸው በፊት፡፡

“ስራችንና የምናቀርበው ውጤት ገለልተኛ፣ ነፃና ለማንም የማያዳላ ነው፡፡ በምርጫው ሂደት ውስጥ ጣልቃ አንገባም፡፡ የኛ ስራ ባስቀማጥናቸው የመታዘቢያ ዘዴዎችና ያለንን ልምድ መሰረት በማድረግ የምርጫውን ሂደት መታዘብ ነው፡፡ እርግጠኛ ነኝ ይሳካልናል ብየ ገምታለሁ፡፡”

ዋና ታዛቢ ቲዝ በርማን ከፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ፣ ከእጩዎች፣ ከመንግስትና ከምርጫ ባለስልጣናት፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮችና ከሚዲያ ተወካዮች ጋር ይነጋገራሉ፡፡ በተጨማሪም ወደተለያዩ ክልሎች በመሄድ ከምርጫ ባለድርሻ አካላት ጋርም ይገናኛሉ፡፡

“በየክልሉ ያሉትን ታዛቢዎቻችንን ለማግኘት ፈልጌያለሁ፡፡ የታዛቢዎቹ ውጤት የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎችን ለመታዘብ ያሉ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ነፃ፣ ተጨባጭና ሀገርአቀፍ ዳሰሳውን ያሳያል ብለን እንገምታለን” ብለዋል ዋና ታዛቢው፡፡

የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ በኢትዮጵያ 2002 ዓ.ም. የሕዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫን ለመታዘብ ትልቅ ቁጥር ያሰማራ የታዛቢ ልዑክ ነው፡፡ ልኡኩ በዋና ተንታኞ ፣ በ90 የረጅም ጊዜ ታዛቢዎችና በ60 የአጭር ጊዜ ታዛቢዎች የተዋቀረ ነው፡፡

የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ታዛቢዎች ጥብቅ የሆነ የስነ ምግባር መመሪያን የሚከተሉ ሲሆኑ በምርጫው ሂደት ጣልቃ አይገቡም፡፡ የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ ምርጫ ታዛቢ ልዑክ አ.አ.አ በ2005 የመንግስታቱ ድርጅት ባወጣው የዓለም ዓቀፍ ምርጫ ታዛቢነት መርሆዎች መግለጫ እና ዓቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች የስነምግባር ደንብን ይከተላል፡፡

የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ ምርጫ ታዛቢ ልዑክ አስካሁን ድረስ ያለውን የምርጫ ሂደት አስመልክቶ ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም. የመጀመሪያ ደረጃ ውጠቱን ይፋ ያደርጋል፡፡ የማጠቃላያውን ውጠት ደግሞ ሁሉም የምርጫው ሂደት ከተጠናቀቀ ከሁለት ወር በኋላ ይወጣል፡፡

ለመገናኛ ብዙሀን ጥያቄዎች ወ/ሮ አግነስ ዶካን ያነጋግሩ

ስልክ፡- +251 (0)920 537 623

E-mail: agnes.doka@eueom-ethiopia.org